

# ሊያ

- ሊያ የላባ ትልቅ ልጁ ነበረች። ሊያ ራሄል የምትባል ታናሽ እህት ነበረቻት። ላባም ራሄልን ለያዕቆብ በሚስትነት ለመስጠት ቃል ገብቷል። ስለሁለቱ እህትማማቾች እንዲህ የሚል በመፅሐፍ ቅዱስ ተፅፎአል፣ "ልያም ዓይነ ልም ነበረች፤ ራሔል ግን መልከ መልካም ነበረች ፊትዋም ውብ ነበረ።" የሰርጉ ጊዜ በደረሰ ጊዜም ላባ ሙሽራይቱን በመቀየር ያዕቆብ ሊያን እንዲያገባት አደረገው። ያዕቆብ ግን በትክክል የሚያፈቅረው ራሄልን ነበር። ላባ ይህን ያደረገበትን ምክንያት ሲገልፅም ባለበት አካባቢ ልማድና ባህል ታላቅ ሳታገባ ታናሽ አታገባምና ነው አለ።

- ያዕቆብ ራሄልን ለማግባት ሰባት አመት አገልግሏል። ስለዚህ ራሄልን ለማግባት ሲል ሌላ ሰባት አመታት ላባን ለማገልገል ተስማማ። ልክ ሊያን ባገባ በሳምንቱም ከራሄል ጋር ጋብቻ ፈፀመ። ሊያ ያዕቆብ እህቷን ልክ ራሄልን እንደሚያፈቅራት እርሷንም እንዲያፈቅራት ናፍቆቷና ጥማቷ ነበር። ነገር ግን ይህ አልሆነም። ሊያ የመጀመሪያ ልጇን ወልዳ ሮቤል ብላ ሰየመችው። ትርጉሙም፣ "እነሆ ወንድ ልጅ" ማለት ነው።ወንድ ልጅ ስለወለደችም ባሏ እንደሚወዳት በጣም እርግጠኛ ነበረች። ሁለተኛ ልጇንም ስምኦን ሰትል ሰየመችው። ትርጓሜውም፣ እግዚአብሔር ይሰማል ማለት ነው። ሶስተኛ ልጇ ስሙ ሌዊ ነበር። ትርጉሙም "የቅርብ ወዳጅ" ማለት ነው። አራተኛ ልጇ ስሙ ይሁዳ ሲሆን ትርጉሙም፣ "እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን፣" ማለት ነው። ከዚያም አምስተኛው ልጅ ይሳኮርና ስድስተኛው ልጅ ዛብሎን ተወለዱ። አሁን ስድስት ልጆች አሏት ባሏንም ታፈቅረዋለች። ሆኖም ያዕቆብ ለሊያ ግድ አልነበረውም። ከጥቂት ጊዜ በኋላም ሊያ ዲና የምትባል ለያዕቆብ ብቸኛ የሆነችውን ሴት ልጅ ወለደችለት። ይህ ሁሉ ሲሆን ራሄል ገና ልጅ አልወለደችም። ያዕቆብ የአማቹን አገር ለቆ ከወጣ በኋላ ወደ ገዛ አገሩ ተመለሰ።

- በዚያም ያጭበረበረውን ወንድሙን ኤሳውን አገኘው። ኤሳው በዚያን ጊዜ አብረውት አራት መቶ ሰዎች ነበሩ። ያዕቆብም ስለቤተሰቡ እጅግ ፈራ። ስለዚህም አገልጋዮቹን ከፊት አደረጋቸው። ከዚያም ሊያንና ልጆቿን አደረገ። በመጨረሻም ራሄልና ልጇ ዮሴፍ ከሁሉ ኋላ አስጊ ባልሆነ ሁኔታ ውስጥ እንዲሆኑ አደረገ። ሊያ አሁንም ያዕቆብ እያደረገ ያለውን ነገር ተመለከተች። ያዕቆብ እርሷንና ልጆቿን ልክ እንደራሄልና እንደ ዮሴፍ ጥበቃ እያደረገላቸው እንዳልሆነ አየች። የኤሳው ቁጣ በተለያዩባቸው ሀያ አመታት ውስጥ በርዶለት ስለነበር በያዕቆብና በቤተሰቡ ላይ አደጋ ለማድረስ ምንም ሀሳብ አልነበረውም።

- ያዕቆብ አስራ ሁለት ወንዶችና አንዲት ሴት ልጅ እስከሚያገኝ ድረስ ቤተሰቡ እያደገና እየሰፋ ሄደ። ራሄልም ዮሴፍና ቢንያም የሚባሉ ሁለት ወንዶች ልጆችን ለያዕቆብ ወለደችለት። እግዚአብሔርም ሊያ የታገሰችውን መከራ ተመልክቶ በጣም ከምታምረው እህቷ ይልቅ አብዝቶ ባረካት። ከልጆቿ የተነሳ ሊያ  ልዩ ስፍራ አላት። ልጇ ሌዊ የእሥራኤል ካህናት በሙሉ የተገኙት ሌዊ ከተባለው ከሊያ ከተወለደው ከያዕቆብ ልጅ ነበር። ከሌዊ ከተገኙት ታዋቂ እስራኤላውያን መካከል ሙሴ፣ አሮን፣ የመጥምቁ ዮሐንስ እናት ኤልሳቤጥ፣ በርናባስና ጴጥሮስ ይገኙባቸዋል። ከይሁዳ ደግሞ ንጉስ ዳዊትና ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ይገኙባቸዋል።

- በእድሜዋ መጨረሻም ሊያ የተቀበረቻው ከያዕቆብ ጎን "ኬብሮን በምትባል በመምሬ ፊት በከነዓን ምድር ባለው እርሻ ባለ ድርብ ክፍል በሆነው ዋሻ ውስጥ" ነው።

ስለሊያ ታሪክ በዘፍጥረት ምዕራፍ 29 እስከ ምዕራፍ 33 ድረስ ባለው ክፍል ውስጥ ማንበብ ትችላላሁ።

http://gardenofpraise.com